# ወቦ ሸማኔው ከጉባኤው አዳራሽ ማህል ቆሟል

ጌታቸው ኃይሌ

ዛሬ ጠዋት (ሚያዝያ 9 ቀን) ኮምፒዩተሬን ስከፍት በጠቅላይ ሚንስትሩ አዳራሽ ታሪካዊ ውይይት ሲካሄድ ደረስኩ። ታሪካዊ ያልኩት ባለሥልጣኖቹ ባሉበትና (በተሳተፉበትም) መድረክ ላይ ስለዲሞክራሲ ግንባታና ተግዳሮቶች እንደዛሬው "ግልጽ" ውይይት ሲደረግ ስላላየሁ ነው። እርግጥ፥ ውይይቱ ሙሉ በሙሉ በግላጭ ላይሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ተሳታፊዎቹን የመረጣቸው መንግሥት ላለመሆኑ ማስረጃ የለኝም። በዚያ ላይ፥ ሲሳተፉ ላያቸው የምፈልጋቸው ሰዎች አልተሳተፉም። ሁለተኛም፥ የባለሥልጣኖቹ መገኘት ጠቃሚ ቢሆንም፥ የተለመደውን የባለሥልጣን ፍራቻ እንዲሰፍን አድርጎት ይሆናል። ሁሉም ነገር ሁለት ገጾች አሉት።

ሌላው ትዝብቴ፥ ብዙዎች ተሳታፊዎቹ  አንዳንድ አስተያየቶችን መንቀፍ እንደትልቅ ነጥብ አቅርበውታል። ግን  ነቃፊውም ተነቃፊውም ራሳቸው መሆናቸውን ልብ አላሉትም። ይህም ሁሉ ቅሬታ እያለኝ፥ ውይይቱን በደስታ ስከታተል ቆይቼ ስለኢትዮጵያ ማጸኢ ዕድል ተስፋ ተሰምቶኛል። ራሱ ውይይቱ በብዙ ሕዝብ ፊት በይፋ መደረጉ ትልቅ ለውጥ ነው። ፈቃድ የሰጠው ባለሥልጣንና አዘጋጆቹ ምስጋና ይገባቸዋል።

ከምላጭ የሳለችው አስተናጋጅ (ሰሎሜ?) ችግሩን (ተግዳሮቱን) ስትገልጽ "The elephant in the room" (በአዳራሹ ውስጥ ያለው ዝሆን) አለችው። እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች (ፈረንጆች ሁሉ ሲሉት ስላልሰማነው "ፈረንጆች እንደሚሉት" አንበል) ይኸን የሚሉት፥ የችግሩ ግዝፈት ዝሆን የሚያህል ሆኖ ሳለ፥ ተመራማሪዎች በማጉያ መነጽር እንኳን ሊያዩት አልቻሉም ሲሉ ነው። የዝሆን ግዝፈት ለችግራችን ታላቅነት ለምሳሌ ይስማማል። ዝቅ ብየ እንደማብራራው፥ የኛን ችግር በወቦ ሸማኔ ብንመስለው ይስማማል። "በአዳራሹ ውስጥ ያለው ወቦ ሸማኔ"።

የውይይቱ ፍሬ ነገር፥ የዲሞክራሲን አስተዳደር ኢትዮጵያ ላይ ለማስፈን የምንችለው መጀመሪያ ሰላምን አውርዶ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ስንቀርጽና ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆነ ስንስማማ ነው የሚል ነበር። የሰላም መቅደም የሁላችንም ጩኸት ነው። ባልተደለደለ ሜዳ ላይ ኳስ ጨዋታ አይቻልም፤ ባልታረሰ መሬት ላይ ዘር አይዘሩም። ወቦ ሸማኔ ኢትዮጵያን የከፋፈላት ዘረኝተኝነት ነው።

አቶ ዳውድ ኢብሳ ኢትዮጵያ ከኛ በኋላ ትኖራለች ሲል፥ ሞቅ ደመቅ ባለ ደረጃ ተጨበጨበለት። ግን የጭብጨባው መጋል ለምን እንደሆነ ግልጽ አይደለም። የኢትዮጵያ መኖር አሥግቶ ስለነበረ ይሆን ወይስ ራሱን የኦሮሞ ብሔርተኝነት ኮከብ ብሎ የሚጠራው ሰው ንግግሩን በዐረቢኛ ስለጀመረ ነው? ማነው ኢትዮጵያን በኢትዮጵያነቷ መኖር የሚያሥጋት? ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ሰው ኢትዮጵያን ሊያጠፋት አይችልም።

የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ስምምነት ማስፈለጉም ተነሥቷል። ወቦ ሸማኔው ያመጣብን ጠንቅ ነው። የኢትዮጵያ ዜጋ ለሆነ ሰው ኢትዮጵያዊ ለመሆን ምንም ዓይነት አዲስ ስምምነት አያስፈልገውም። ዛሬ ዓለም በሀገር ደረጃ ተከፋፍላ ስም የወጣላቸው ሀገሮች ወጥቷታል። እርግጥ፥ አንድ ሰው ሀገር-አልባ (stateless) ለመሆን ከፈለገ ይችላል። ግን የሚችለው፥ የተወለደበትን ሀገር ለቆ፥ ወደ አልተወለደበት ሀገር ሄዶ፥ ሲኖር ነው። ኢትዮጵያዊነቱ ከታወቀ ምድር ላይ እየኖሩ በኢትዮጵያዊነት እንስማማ ማለት አይቻልም። የቀረበ ምግብ እየኮመኮሙ፥ በቀረበው ምግብ እንስማማ አይባልም።  የሚቻለው ከሚናፍቁት ሀገር ሄዶ ዜግነትን መለወጥ ወይም አንድ ሕዝብ ባልያዘው አዲስ ምድር ላይ ሰፍሮ፥ ለሰፈረበት ምድር እገሌ የሚል ስም ለመስጠት ሲስማማ ነው። በአሁኑ ሁኔታ ኢትዮጵያ ላይ ያለው አብዛኛው ሕዝብ ሐሳቡን ካልተቀበለው ከማን ጋር ነው ድርድሩ የሚካሄደው? ታሪክ የሠራችን ኢትዮጵያን ለማን ስንል ለድርድር እናቀርባታለን?

አዲስ እና አሮጌ ኢትዮጵያዊነት የለም። እኛ ኢትዮጵያን የፈጠሯት ኢትዮጵያውያን ልጆቻቸው እስካለን ድረስ ኢትዮጵያዊነት ይኖራል። ታሪካችንም በማይፋቅ በማይለቅ ቀለም ተመዝግቧል። በድንጋይ ላይ

ተቀርጿል፤ እንኰራበታለን፤ መኵሪያችንን እናከብራለን፥ እናስከብራለን። የታሪክ መጻሕፍታችን ከቤተ መጻሕፍት ለማጥፋት፥ ያልሆነ ታሪክ ሊጽፉላት የሞከሩ ጠላቶች ተነሥተው ነበር፤ አልቀናቸውም።

እርግጥ፥ ፖለቲካው ሊለወጥ ይችላል። ለምሳሌ፥ ኢትዮጵያ የንጉሥ ሀገር መሆኗ ቀርቷል፤ እሷ ግን አልቀረችም። ለጥቂት ዘመናት ከመምዕላይ እጅ ወድቃለች፤ ግን አለች። ፖለቲካው ይቀየራል፤ ኢትዮጵያ ግን ትኖራለች። ኢትዮጵያንና ታሪኳን ለመለወጥ የሚፈልግ መተላለቅን የሚጋብዝ ነው። የአሁኑ ጉባኤ ዲሞክራሲ የሚሰፍንበትን መንገድ ለመፈለግ ነው። ከቀናው በማትለወጠው ኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ ይደረጋል። ያ ቀን ሕልማችን የደረሰበት ቀን ይሆናል።

የዲሞክራሲ ሥርዓት ሲገነባ ከሚገጥሙ ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ያለው ወቦ ሸማኔ መሆኑን ልብ ያለው የለም። (ወቦ ሸማኔ በግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ነብር እንደሚመስል እንጂ፥ በቅርብ ጊዜ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ውስጥ ገብቶ ኖሮ፥ የ *ዘሐበሻ* ዜና ዘጋቢዎች በፎቶግራፍ እስኪያሳዩን ድረስ መልኩ ምን እንደሚመስል አላውቅም ነበር።) ዋናው ቁም ነገር፥ ወቦ ሸማኔን ከዝሆን የሚለየው ሰው-በላ መሆኑ ነው። በሰው በላው ወቦ ሸማኔ የምመስለው ችግራችን የጎሰኝነት ፖለቲካ ነው። በውይይቱ ከሚሳተፉት ውስጥ አንዱም ስሙን ሲጠራው አልሰማሁም። ሀገራችን ከንጉሣዊ አስተዳደር ወደ ዲሞክራሲ ሥርዓት ለመሸጋገር አንድ ሁለት እርምጃ እንደተራመደች፥ የጎሰኝነት ፖለቲካ ጠልፎ ጣላት።

የአሁኑ የውይይት አጀንዳ ይህን ወቦ ሸማኔ ለማስወገድ መስማማት ላይ ማተኰር ሲገባው፥ የማስተናገጃ መንገድ ፍለጋ ሆነ። ከተቺዎቹ አፍ ሲወጣ የሚሰማው፥ "እነ  እገሌን እግዚአብሔር ይይላቸው፥ እገሌን ነፍሱን አይማረው፥ ተማሪዎቹ ጉድ አደረጉን፥ . . . ጎሰኝነትን በሕዝቡ አእምሮ ዘሩበት" ማለት ብቻ ሆነ። "ና ውጣ" የሚልልን ጀግና ጠፋ። ከሥልጣን ውጪ የሆኑ ሰዎች ብዙ ጊዜ እንደጻፉት፥ ፖለቲካንና ጎሰኝነትን የሚያገናኝ ጉዳይ የለም። የሚያገናኛቸው የሰው ልጅ አንጎል ብቻ ነው። ጎሰኝነት እንደ ሃይማኖት ከፖለቲካ ውስጥ እንዳይገባ የሚከለከል ባህል ነው። አንድ ሰው ለፖለቲካ ጉዳይ ሲፈለግ፥ ሃይማኖቱ ምንድን ነው እንደማይባል፥ ጎሳው ምንድን ነው አይባልም። ጎሳ የሃይማኖትን  ያህል የግል ነው። መፍትሔው ጎሰኝነትን ከፖለቲካ ማለያየት ነው።

"ጎሰኝነት" የምለው የዘመኑ ፖለቲከኞች "ብሔርተኝነት" የሚሉትን ነው። የፖለቲካው ስሕተታችን ከዚህ ማማታት ይጀምራል። "ብሔር" ማለት "ሀገር" ማለት ነው። አንድ ሰው "ብሔርተኛ ነው" ማለት በመሠረቱ "ሀገሩን ይወዳል" ማለት ነው። አሁን ግን "ጎሳውን እንደ ሀገር ወይም ከሀገር አብልጦ ይወዳል" ማለት ሆኗል። ይህ "ብሔርተኝነት" የሚባለው ጎሰኝነት በሀገር ደረጃ ከታየ የሀገር አንድነትን ከአደጋ ላይ ይጥላል። ጎሰኝነትና ሀገረኝነት የማይጋቡ ዘመዳሞች ናቸው። ሳይጋጩ በሰላም በጉርብትና እንዲኖሩ እድምተኞቻቸውን  ልንመክራቸው ይገባል። ከተጋጩ ማሸነፍ የሚገባው ሀገርተኝነት ነው። ከሀገር በላይ ነፋስ። "በአዳራሹ ውስጥ ያለውን ወቦ ሸማኔ" ከፖለቲካ ውስጥ አውጥቶ እቦታው ላይ በክብር ማስቀመጥ የሀገር ወዳዱ ሁሉ ግዴታና ዘመቻ መሆን አለበት።

"የጎሳ የክብር ቦታ" በጎሳው ቤት ውስጥ ነው።  ቤቶቹ ትግራይ፥ኦሮሞ፥ ጉራጌ፥ ሲዳማ፥  ጋምቤላ፥ ወላይታ፥ . . . ይባላሉ።  እነዚህና ሌሎቹ ነገዶች ወይም ጎሳዎች ከመንግሥት ራቅ ብለው ባህላቸውን ማዳበር ይችላሉ። የተራድዖ ድርጅት ማቋቋም ይችላሉ። ጎሰኝነት በመንግሥት ጉዳይ፥ መንግሥት በጎሳ ጉዳይ እንዳይገቡ በሕግ መከልከል አለባቸው።

የአማራ ሕዝብ ከነዚህ ይለያል። አማራ ሕዝብ እንጂ፥ ነገድ ወይም ጎሳ አይደለም።  አማራ አለ፤ ግን  ያለው በሕዝብነት እንጂ ጎሳ ወይም ነገድ ሆኖ አይደለም። "የአማሮች ጎሳነት" የሌሎቹ ጎሳዎች ጎሳነት ዓይነት አይደሉም። አማሮች በጎሳነት ለመደራጀት ወደኋላ የቀሩበት ምክንያት አቶ ዳዊድን የገረመው ምክንያቱ ስለጸነነበት ነው።  አማሮች የተፈጠሩት ሌሎች ጎሳዎች/ነገዶች በተፈጠሩበት መንገድ አይደለም። **አማሮች ጎሳቸውን ትተው፥ ሀገረ መንግሥትን፥ "ሁሉን ትተን ተከተልንህ" ያሉ ከየጎሳው የተጠራቀሙ ሕዝብ ናቸው።**

አማሮችን እዚህ ያደረሳቸው ረጅሙ የሀገራችን ታሪካዊ ሂደት ነው። ለማብራራት አማሮችን በዓባይ ወንዝ ውሓ ልመስላቸው። ከጣና ባሕር የሚነሣው የዓባይ ውሓና ባሕረ ኢያሪኮ (Mediterranean Sea) የሚገባው የዓባይ ውሓ አንድ አይደሉም። ዓባይ የኢትዮጵያን ምድር ለቆ እስኪወጣ ድረስ ብዙ የኢትዮጵያ ወንዞች ውሓቸውን ለሱ አስረክበዋል። ያም ሆኖ፥ ውሓው የዓባይ ውሓ ነው የሚባለው። ከጣና የሚወጣው የውሓ መጠን ከባሕረ ኢያሪኮ ከሚገባው ውሓ ጋር ቢተያይ ኢምንት ነው።

አማራ የሚባል ነገድ ነበረ (ወሎ ውስጥ)። ግን የዛሬው የአማራ ሕዝብ ሁሉም የነገደ አምሐራ ልጆች አይደሉም። አብዛኞቹ ጎሳቸውን ትተው አማራ (በዚያ ላይ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን) የሆኑ ልጆች ናቸው። ይኸ ዓይነት መሸጋሸግ በሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ላይ ደርሷል። በተለይ ኦሮሞች ብዙዎችን የሌላ ነገድ ሰዎች በግድም በውድም ኦሮሞዎች አድርገዋቸዋል። ስለዚህ ነው፥ “እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ብዙ ጎሳዎች ነው” የሚባለው። ግን አማሮች ላይ የደረሰው ዓይነት ሚዛን የደፋ መሸጋሸግ በማንም ጎሳ/ነገድ ላይ አልደረሰም። የመሸጋሸጉም ምክንያት የተለየ ነው። ወደ አማራነት መሸጋሸግ የመጣው ቋንቋቸው አማርኛ በተጫወታቸው ሁለት ሚናዎች ነው፤ አንደኛ፥ አማርኛ የመንግሥቱ ከሕዝቡ ጋር መገናኛ ሆነ። ሁለተኛ፥ የዕውቀት መገብያ ሆነ። በዚህ ሂደት የጎሳ ሰዎችም ጎሳቸው ለቀው ወደአማራነት መንሸራሸር ብቻ ሳይሆን፥ ሳይለቁ (ማለት ወደ አማራነት ሳይሸጋሸጉ) አማርኛን ከጎሳቸው ውጪ ካለው ሕዝብ ጋር መገናኛ አደረጉት። አማርኛ አገናኘን፤ አማርኛ ዕውቀት መገብያ ሆነን።

“አማርኛ ዕውቀት መገብያ ሆነን” ስል ብዙ ሰው የሚያስበው በመንግሥት ትምህርት ቤት ትምህርት የሚሰጠው በአማርኛ መሆኑን ማስታወሴ ይመስላቸዋል። እሱን ማለቴ አይደለም፤ እሱንማ መንግሥት በሌሎች ጎሳዎች ላይ አድልዎ እንደሠራባቸው ይቈጥሩታል። እሱን በኋላ እተቸዋለሁ። አሁን የምናገረው ሲወርድ ሲዋረድ እኛ ዘንድ ስለደረሰው ሀገር-በቀል ሥርዓተ ትምህርት ነው። ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የትምህርት ሥልጣኔ ነበራት። ሲጀመር፥ ትምህርቱ የክርስትና ሃይማኖት፥ አስተማሪዎቹ አግዓዝያን ነበሩ። ቋንቋቸው ግዕዝ ነበረ፤ አግዓዝያን የተለያየ ጎሳ በመሆን ሲጠፉ፥ ሥርዓቱን ትግሬዎችና አማሮች ወርሰው ቀጠሉ።

ቀስ በቀስ አማሮች ተተኩ። ማለት መምህራኑ **አማርኛ ተናጋሪዎች**፥ የአማራ ሳይንት (የዛሬ ወሎ)፥ የሸዋ፥ የጎንደር፥ የጎጃም ሰዎች ሆኑ። ትምህርቱን በተማሩት በግዕዝና አፋቸውን በፈቱበት በአማርኛ አደረጉት። ተማሪውም አብዛኛው አማራና ትግሬ ሲሆን፥ ከሌላ ጎሳዎች የመጡ ጥቂት ልጆችም ነበሩ። ከሌላ ጎሳዎች በብዛት አለመምጣታቸው ሀገራዊ ጉዳት አለው። ግን ላለመምጣታቸው ወቀሳ የሚያስከትል ከሆነ፥ ተጠያቂዎቹ አስተማሪዎቹ ወይም ቤተ ክህነት ሳይሆኑ፥ ባህሉ ነው። በባህሉ መሠረት፥ አንድ አስተማሪ ራሱን ቀጥሮ (self-employed) አስተማሪ ይሆናል። ልጆች አስተማሪ አለ የሚባልበትን ቦታ ፈልገው ሄደው ይመዘገባሉ። የትምህርት ባህል በሌለበት አካባቢ አስተማሪ ስለማይኖር የዚያ አካባቢ ልጆች በትምህርት ማጣት ተጎድተዋል።

ይኸ ይሆን የነበረው መንግሥት ዓለማዊ ትምህርት ማስተማርን አስፈላጊ ሆኖ ባላገኘበት ዘመን ነበረ። አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ያቋቋመው ሥርዓተ ትምህርት ሌሎቹ የጥንት ሀገሮች የወሰዱትን ይመስላል። የትምህርት ሥልጣኔ ባላቸው ሀገሮች ሁሉ ትምህርት ያደረገው የእድገት እርምጃ ከመንፈሳዊ ትርምህርት ወደ ዓለማዊ ትምህርት መሸጋገር ነው። ቋንቋውም ያው መንፈሳዊው ትምህርት ይሰጥበት የነበረው ቋንቋ ነው። የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ወደ ዓለማዊ ትምህርት ሲሸጋገር ከሌላው ሀገር የተለየ መንገድ አልቀየሰም። መሸጋገሪያው በአማርኛ እንዲሆን የታሪክ ሂደት አስገድዷል።

እዚህ ላይ አንድ በገለልተኝነት የሚመለስ ጥያቄ ልጠይቅ፤ የትምህርታችን መሸጋገሪያ አማርኛ ካልሆነ በሌላ በምን ቋንቋ መሸጋገር ነበረበት? በዚያን ጊዜ፥ በሌሎቹ ቋንቋዎች ሁሉ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን እንኳን ማንም ልብ አላለው። ልብ ቢለውስ፥ በየትኛው ቋንቋ አስተምሮ፥ በሌሎቹ ኢያስተምር? አማርኛን የማስተማሪያ ቋንቋ ማድረግ አማራጭ የሌለው የታሪክ ውሳኔ ነው። ሁሉም በቋንቋው ላይ አንድ ተጨማሪ ቋንቋ (አማርኛ) ተምሮ ቢማሩበት ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም። አማራም አያደርግም። ዛሬ እንግሊዝኛ

የምንማረው እንግሊዝ ለመሆን ሳይሆን፥ ዕውቀት እንድንቀስምበትና ቋንቋቸውን ከማናውቀው ሰዎች ጋር እንድንገናኝበት ነው። ስሕተቱ በሌሎቹ ቋንቋዎች ማስተማር በተቻለ ጊዜ መከልከሉ ነው።

ለሀገር አንድነትና ለመበልጸግ ከታሰበና ከተቻለ፥ ትምህርት በየትኛውም ቦታ በአማርኛና በራስ ቋንቋ መሆኑ ሊደገፍ ይገባል። የፌዴራሉ አባል ክፍለ-ሀገሮችም በአማርኛ (በመንግሥቱ ቋንቋ) እና በሌላ በፈለጉት ቋንቋ ቢሠሩ ጥቅም አለው። የመንግሥቱን ቋንቋ ማወቅ ጥቅሙ ሁለት ነው፤ አንደኛ፥ ሁላችንም በአንድ ቋንቋ እንገናኛለን። ሁለተኛ፥ በአማርኛ ላይ የሚጨመረውን ቋንቋ የማያውቁ ብዙዎች ስለሆኑ፥ ሁሉም በአማርኛ ይገናኙበታል። የመንግሥቱና የፌዴራሉ አባል ክፍለ-ሀገሮች የሥራ ቋንቋቸው የመንግሥቱ ቋንቋ ቢሆን፥ ሁሉም አንድ ቋንቋ ብቻ እያወቀ የመንግሥቱ ተሳታፊ ይሆናል።

የመንግሥቱን ቋንቋ የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከፈለገው የኢትዮጵያ ክፍለ-ሀገር ሄዶ ቢኖር ባይተዋር አይሆንም። ባለበት ሀገር አስተዳደር ውስጥ እኩል ተሳታፊ ይሆናል። ትልቁ የዲሞክራሲ ምሳሌ በሚባለው በአሜሪካ የሆነው ይህ ነው። ሁሉ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ነው፤ ግን ነገደ እንግሊዝ አይባልም። አብዛኛው ሕዝብ ነጭ ነው። ግን ነገደ ነጭ የለም። ያለው ከነጩ ሁሉ የተውጣጣ አንድ ነጭ ሕዝብ ነው። አማራ የሚባል ብዛት ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ አለ፤ ግን የአማራ ነገድ የለም። ካስፈለገ የመንግሥት ነገድ እንበላቸው። የመንግሥት ነገድ ስለሆኑ፥ መንግሥት የሚሠራበትን ቋንቋ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አድርገውታል። የአማራ ሕዝብ ከማንኛውም ጎሳ ይበልጥ መንግሥት ባለበት ቦታ ሁሉ የሚገኘው የመንግሥት ነገድ ስለሆኑ ነው። ካልፈለጉ የግድ ተጨማሪ ቋንቋ መማር አያስፈልጋቸውም። አያቶቻቸው ወደ አማራነት መሸጋሸጋቸው ጠቅሟቸዋል።

"መላው ዓለም አንድ ቋንቋ ብቻ ነበረው። እግዚአብሔርም አለ፤ እነሆ ሰዎቹ አንድ ወገን ናቸው። ሁሉም በአንድ ቋንቋ ይግባባሉ። ሰማይ-ጠቀስ ግምብና ከተማ መሥራት ጀመሩ። ያሰቡትን ሁሉ ከማድረግ የሚያቆማቸው የለም። ኑ እንውረድና አንዱ የሌላውን ነገር እንዳይሰማ ቋንቋቸውን እንደበላልቀው"

ጌታችን ለእርግማን የፈጠራቸውን ብዙ ቋንቋዎችን ለበረከት አድርጎ፥ በአንድ ቋንቋ እንድንግባባ የጀመርነውን ይባርክልን ዘንድ እንጸልይ።